# እውነተኛ

# አምልኮ

**1988 ዓ. ም.**
**1996 እ. ኤ. አ.**

ከዶክተር ዓለሙ ቢፍቱ

ይህን
መጽሐፍ
ያለ ደራሲው
ፈቃድ ማባዛት
ወይም መልሶ ማሳተም
በሕግ የተከለከለ ነው።

Copyright Alemu Beeftu, February, 1996

All Rights Reserved.

PRINTED IN THE U.S.A

ይህን

መጽሐፍ

በእውነተኛ አምልኮ

እግዚአብሔርን በመዝሙርና በቅኔ

ለሚያገለግሉ መዘምራን ሁሉ አበረክታለሁ።

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| መቅድም | 06 |
| 1▸ እግዚአብሔርን የማምለክ ምስጢር | 11 |
| ◊ በምስጋና የሚገለጽ አምልኮ | |
| ◊ በጸሎት መልክ የሚቀርብ አምልኮ | |
| 2▸ በስግደት የሚገለጽ አምልኮ | 20 |
| 3▸ የምናመልከውን ማወቅ | 27 |
| ◊ የአምልኮአችን መሠረት | |
| ◊ የአምልኮአችን ትኩረት | |
| 4▸ ለምን እንደምናመልክ ማወቅ | 34 |
| ◊ በምን እንደምናመልክ ማወቅ | |
| ◊ እንዴት እንደምናመልክ ማወቅ | |
| 5▸ የግል አምልኮ | 45 |
| 6▸ የቤተሰብ አምልኮ | 51 |
| 7▸ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ | 58 |
| ◊ ለቤተ ክርስቲያን አምልኮ ዝግጅት | |
| 8▸ የአምልኮ መሪዎች ዝግጅት | 63 |
| 9▸ ለውሳኔ የሚያበቃ የአምልኮ ሕይወት | 73 |
| ◊ የዳዊት ሕይወት | |
| ◊ የዳዊት መረዳት | |
| ◊ የዳዊት ውሳኔ | |
| 10▸ ሊቀበል ይገባዋል - ክፍል አንድ | 87 |
| 11▸ ሊቀበል ይገባዋል - ክፍል ሁለት | 96 |

# ምስጋና

እርሱን በፈጣሪነቱና በአዳኝነቱ አውቄው እንዳመልከውና እንዳገለግለው በደሙ ዋጅቶ ልጁ ላደረገኝ አምላኬና አባቴ ክብርና ምስጋና ይሁን። በአሁኑ ዘመን በሕዝቤ መካከል የዝማሬንና የቅኔን ምንጭ በማፍለቅ አንደበታችንን በምስጋና ለሞላው አምላክ ለዘላለም ክብር ይሁን።

በዚህ አገልግሎት በጸሎትም ሆነ ሃሳብ በመስጠት አብረውን ለቆሙ ወገኖች ሁሉ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ እላለሁ። በተለይም ይህን መጽሐፍ ታይፕ በማድረግና በሌሎችም አገልግሎቶች በምክሯም ሆነ በጸሎቷ አብራኝ ለጌታ ሥራ ስለምትተጋ ስለ ባለቤቴ ስለ ገነት ያዕቆብ አምላኬን አመሰግነዋለሁ።

እንዲሁም ደግሞ መጽሐፉን አንብበው ጠቃሚ ምክራቸውን ያበረከቱትን አቶ ጌታቸው ጭኮን፣ አቶ የኋላሸት ካሣን፣ አቶ መንግሥቱ ለማን፣ ዶ/ር ቤተ መንግሥቱን፣ አቶ ሰለሞን አሻግሬን፣ ዶ/ር ቶለሳ ጉዲናን፣ ወንጌላዊ ሃብቴ አዳነን፣ አቶ ንጉሤ ቡልቻንና ወ/ት ጥሩወርቅ መስፍንን ከልቤ ላመሰግናቸው እወዳለሁ። ጌታ አሁንም በይበልጥ ሕይወታቸውንና አገልግሎታቸውን እንዲባርክ ጸሎቴ ነው።

# መቅድም

እግዚአብሔር አምላኪዎችን ይፈልጋል። ሊመለክ የሚገባው በእውነትና በመንፈስ ብቻ እንደሆነ ቃሉ ያስረግጥልናል። ከዚህም በላይ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው አምልኮ እርሱን እንደ አምላክነቱ አውቀን በምንም ሳንወሰን የምናቀርብለት ስግደት ነው። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አራት ላይ ጌታ ኢየሱስ ሳምራዊቷን ሴት ሲያናግራት የዚህን ዓይነት አምልኮ አስፈላጊነት ገልጾላታል። በዚህ ተራራ ላይ እናመልካለን ስትለው – "እናንተ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ።... እኛ ግን መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን" አላት። አዲስ ነገር መምጣቱን ሲያመለክታት ለማያውቁት የሚሰግዱበት ጊዜ እንደሚያበቃ ገለጸላት። ደህንነትን ተስፋ እያደረጉ ለሚሰግዱትም የደህንነት እራስ እርሱ ራሱ ስለሆነ ተስፋው አሁን እንደተፈጸመ አረጋገጠላት። ከዚህ በኋላ ያለው አምልኮ ስፍራና ሁኔታ ሳይገታው በእውነትና በመንፈስ የሚሆንበት ጊዜ መድረሱንና ወቅቱም አሁን እንደሆነ ነገራት። "በእውነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን የምታመልኩበት ጊዜ ይመጣል ያም ጊዜ አሁን ነው።" (ዮሐ. 4:21-24) (በሕያው ቃል) በሌላ አባባል ዛሬ የያዛችሁትን ውጫዊ የአምልኮ ልማድና መንገድ ትታችሁ በእውነትና በመንፈስ ወደምታመልኩበት ሕይወት ትገባላችሁ አላት።

እንግዲህ ስለ አምልኮ ስናስብ ያለንበት ጊዜ እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንደሚገባን የምንገነዘብበት ወቅት እንደሆነ ማስተዋል ይኖርብናል። ጌታም ጊዜው አሁን ነው ብሎአልና። በተጨማሪም እግዚአብሔር አብ እንዴት ዓይነቶቹን አምላኪዎች እንደሚፈልግ መረዳት ያስፈልገናል።

የመንፈስና የእውነት አምልኮ ከግል ሕይወት ይጀምራል። ይህ ዓይነቱ አምልኮ በግል ጌታን ከማወቅና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር

ሕብረት ከማድረግ የሚፈልቅ ነው። አምልኮአችን በቦታ፣ በአካባቢና በውጫዊ ነገሮች ሳይለካና ሳይገደብ፣ በጊዜውም አለጊዜውም ውስጣችን በፈሰሰው መንፈስ፣ መንፈስ ከሆነው ጌታ ጋር እውነተኛ ግንኙነት ማድረግ ያስፈልገናል። ይህ ዓይነቱ ግንኙነት የአንድነትን አምልኮ ከማጠንከሩም በላይ ያበለጽገዋል።

አምልኮ እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ሊያደርግና ሊፈጽማቸው ለሚፈልጋቸው ነገሮች በሮችን ይከፍታል። ለምሳሌ:-

- ሰዎች በአምልኮ ውስጥ ሊቀቡ ይችላሉ። (1ሳሙ. 16:5-13)
- የእግዚአብሔር ድምጽ ላለንበት ሁኔታ በአምልኮ ጊዜ ሊመጣ ይችላል። (2ነገሥ. 3:15)
- ዙሪያችንን የከበበን ጠላት በአምልኮ ውስጥ ስንገባ ሥራው ሁሉ ይፈርሳል። (2ዜና 20:22)
- በመንፈስ ሆነን ስናመልክ እስራት ሁሉ ይፈታል። (ሐዋ. 16:25-26)

እንግዲህ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ከሚሻው ትልቁ ነገር በእውነትና በመንፈስ የሆነ አምልኮ ነው። እግዚአብሔርን በመንፈስ ካላመለክነው አናውቀውም ማለት ነው። ካላወቅነው ደግሞ እንደሚገባ ልናመልከው አንችልም። "እውነተኛ አምልኮ" የሚለው ይህ መጽሐፍ እንደ እግዚአብሔር ቃል እውነተኛና በመንፈስ የሆነውን እግዚአብሔር የሚሻውን አምልኮ በግል፣ በቤተሰብና በቤተ ክርስቲያን ደረጃ የምናውቅበትን መመሪያን ይሰጠናል። የዚህ መጽሐፍ ትኩረት ያለንበት ዘመን እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የአምልኮን መንፈስ ያፈሰሰበት ወቅት ስለሆነ መንፈስ ቅዱስን በማያሳዝንና እውነትን በማይለቅ መንገድ ማምለክ እንድንችል ነው።

ወንጌላዊ ሃብቴ አዳነ

# መግቢያ

የአምልኮ ታላቅነት ከውስጥ የመነጨ ለአምላክ ብቻ የሚገባ የፍቅር፣ የአክብሮትና የምስጋና መግለጫ መሆኑ ነው። በሌላ በምንም መንገድ መግለጽ የማይቻል የጠለቀ ውዳሴ በአምልኮ ይገለጻል። እግዚአብሔርን ባወቅነው መጠን አምልኮአችን ከውጫዊ ሥርዓት አልፎ በሁለንተናችን ለእርሱነቱ የምናቀርበው የተቀደሰ መሥዋዕታችን ይሆናል። የልባችን ዓይኖች በጸጋው ተከፍተው እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ማለትም:-

- በፈጣሪነቱ
- በሁሉን ቻይነቱ
- በመሐሪነቱና በፍቅሩ መጠን ወዘተ.

መረዳት ስንጀምር ከውስጣችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በአምልኮ ብቻ የሚገለጽ የውዳሴ፣ የቅኔና የምስጋና ምንጭ መፍለቅ ይጀምራል። ይህ በጌታ ጸጋና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚወጣ አምልኮ የእግዚአብሔርን ልብ ደስ ከማሰኘቱም በላይ ለአምላኪው የልብን ደስታና የሕይወትን እርካታ ያበዛለታል። የመንፈስንና የስሜትን ፈውስ ያመጣል። እግዚአብሔርን የማወቅ፣ የማክበር፣ የመፍራት፣ የመውደድንና ለእርሱ ክብርና ምስጋና ብቻ የመኖርን ናፍቆትና ፍላጎትን ያሳድጋል።

ከዚህ ሁሉ ጋር በእውነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን ማምለክ ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ያጠነክርልናል ሕልውናውን በዕለታዊ ኑሮአችን መለማመድ ስለምናዘወትር መንፈሳዊ ዕድገታችን ሚዛናዊና ሁልአቀፍ ይሆናል። ይህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ዕድገት ከራሳችን ነጻ በመሆን በእርሱ ላይ ማረፍንና በእርሱ

መታመንን ከአእምሮ እውቀት ወደ ተግባራዊነት ያመጣዋል። በዚህ መንፈሳዊ ሂደት ውስጥ በእርሱ ማመንን በእርሱ ወደ መታመን ደረጃ ከፍ ስለሚያደርገው የእምነት ጉዞአችን እርሱን ደስ ያሰኘዋል። የቅዱሳን ሁሉ ጥሪ በእምነት እርሱን ደስ ማሰኘት ነውና።

እንግዲህ በአጠቃላይ በመንፈስና በእውነት ለእግዚአብሔር ስለሚቀርበው አምልኮ ስናስብ:- እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚችል ማን እንደሆነ፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አምልኮ ምን ዓይነት እንደሆነ፣ እግዚአብሔር ለምንና እንዴት እንደሚመለክ ማስተዋል ይገባናል።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ የእግዚአብሔር ቅዱሳን የተቀደሰውን አምላክ ለማምለክ የተሰጣቸው ቀዳሚና የከበረውን ጥሪ ቸል በማለት የአምልኮን መልክ ይዘው ኃይሉን እንዳይዘነጉና ከውጫዊው ይበልጥ ለውስጣዊው ነገር እንዲጠነቀቁ ለማሳሰብ ነው።

በአገልግሎት ምክንያት ወደ ብዙ አገሮች እሄዳለሁ። በተለያዩም ሕዝብ መካከል አገለግላለሁ። ነገር ግን በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ እንደ ፈለቀው ዓይነት የዝማሬና የቅኔ ምንጭ በየትም አገር አላየሁም። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ምሕረቱን ለመግለጽና በውዳሴና በምስጋና ለእውነተኛ አምልኮ ወደ ደጁ ለመቅረብ ብቻ ሳይሆን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብተን ክብሩን እንድናይና ምድራችንም በእርሱ ታላቅነት እንድትሞላ ነው።

አምልኮ የሰውን ልብ ለእግዚአብሔር ይከፍታል፣ የእግዚአብሔርን ልብ ለሰው ይከፍታል። የአምልኮ መሠዊያ የእግዚአብሔርን ሕልውና ብቻ ሳይሆን በረከቱን በከፍተኛ ድምጽ ይጠራል። “የጭቃ መሠዊያ ሥራልኝ፣ የሚቃጠለውንና

በማሳስብበት ስፍራ ሁሉ ወደ አንተ መጥቼ እባርክሃለሁ።”
(ዘጸ. 20:24)

የአምልኮ ደመና የበረከት ዝናብ ያመጣል። ከሁሉም በፊት አምልኮን ማስቀደም ለእግዚአብሔር ክብርን ለእኛ ደግሞ ታላቅ በረከትን ያመጣል። “አምላካችሁንም እግዚአብሔርን ታመልኩታላችሁ፣ እርሱም እህልህንና ውኃህን ይባርካል፤ በሽታንም ከመካከልህ አርቃለሁ።” (ዘጸ. 23:25) ያለው ጌታ የታመነ ነው።

ዶክተር ዓለሙ ቢፍቱ

# ም ዕ ራ ፍ 1

## እግዚአብሔርን የማምለክ ምሥጢር

እግዚአብሔርን ማምለክ ጥልቅ የሆነ ታላቅ ምሥጢር አለው። እግዚአብሔርን ማምለክ ምን እንደሆነ ለማወቅ በቅድሚያ እውነተኛ አምልኮን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።

አምልኮ እግዚአብሔርን በማንነቱና ስለማንነቱ-የታላቅነቱ፣ የጌታነቱ፣ የኃያልነቱ ክብር ሲታየን የምናቀርበው፣ የፍቅርና የአክብሮት ስግደት ነው። እግዚአብሔርን ስለማንነቱ ስናመልክ በመንፈሳችን ከእርሱ ጋራ እውነተኛ ሕብረት ስለምናደርግ ነፍሳችን በክብሩ ሙላት ትዋጣለች ልባችንም የደስታን ምንጭ ያፈልቃል። እንግዲህ እውነተኛ አምልኮ ማለት ለእግዚአብሔር የሚገባውን ምስጋናና ውዳሴ፤ ሙገሳና ስግደት ሁሉ በቃል፣ በተግባር፤ በቅድስናና በታላቅ አክብሮት ማቅረብ ማለት ነው። ምስጋናና ውዳሴ፤ መፈራትና መከበር፤ ቅድስናና ንጽሕና ለእርሱ ስለሚገባው ይህንን ዓይነት መሥዋዕት ሁሉ ይዘን ወደ ልዑል እግዚአብሔር ፊት በጸጋው መቅረብ በእርግጥ እውነተኛ አምልኮ ነው። ይህ ዓይነት ከልብ የመነጨ የአምልኮ መሥዋዕት በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል።

እውነተኛ አምልኮ ለቅዱሱ፣ ለጻድቁና ለልዑሉ እግዚአብሔር የሚገባውን ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በክርስቶስ ጸጋ ማቅረብ ነው። ይህ እውነት ከሆነ፣ በክርስትና ሕይወታችን ከምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ይልቅ

የቀደመውንና የበለጠውን ሥፍራ መያዝ የሚገባው አምልኮ ነው ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ማንነት ከተረዳን በኋላ፤ በቅድሚያ "አምልኮዬ ይገባዋል" እንላለን። ከዚያም በኋላ ዝማሬዬ፤ ምስጋናዬ፤ አክብሮቴ፤ ገንዘቤ፤ ጉልበቴና ሁሉ ነገሬ ይገባዋል ማለት እንችላለን። ለእግዚአብሔር የማይገባውን በሕይወታችን ማቅረብ እግዚአብሔርን ከመሳደብ አይተናነስም። እግዚአብሔር አምልኮ ይገባዋልና እውነተኛ አምልኮን ይፈልጋል። የሚገባውን አለማቅረብ ወይም ማሳነስ ደግሞ እግዚአብሔርን መናቅ ይሆናል። ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ ለጠያቂዎቹ መልስ ሲሰጥ «የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር» ብሎ የተናገረው። የቄሣር ለእግዚአብሔር ለመሆን ብቃት የለውም። የእግዚአብሔር ደግሞ ለቄሣር ወይም ለእኔና ለእናንተ ሊሆን አይገባም። አምልኮም የእግዚአብሔር ብቻ ከሆኑት ለማንም ለሌላ ከማይገቡት ነገሮች ዋነኛው ነው።

እውነተኛ አምልኮ የነፃ ሕይወት ምልክት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ነፃነት የሌለው ሰው ሊያመልክ አይችልም። ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ወደዚህች ምድር የመጣው እኛን ነፃ ለማውጣት ነው። ስለዚህ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ታጥበን ነፃ ከወጣን በኋላ በመጀመሪያ የምናደርገውና በነፍሳችን ውስጥ የሚከናወነው ነገር መስበክ ወይም በጸጋ ስጦታዎች መጠቀም ሳይሆን አምልኮ ነው። ስለዚህ አምልኮ የነፃ ሕይወት ምልክት ነው። ብዙ ጊዜ ሳናውቀው በሞኝነት የምናልፈው ነገር ቢኖር ጠላት የአምልኮ ሕይወታችንን ማሰሩን ነው። በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ታስረን እያለን ልንሰብክ እንችላለን፤ ልንዘምር እንችላለን፤ ብዙ ነገር ልናደርግ እንችላለን፤ ነገር ግን ልናመልክ አንችልም። በእውነትና በመንፈስ ካላመለክን ደግሞ ሌላው ድርጊት አገልግሎትም ቢሆን ቁምነገር አይኖረውም።

እግዚአብሔር የሚፈልገውና ልቡን የሚያረካው ቃሉን መስበኬና መዘመሬ ሳይሆን በቅድሚያ እርሱን ማምለኬ ነው። እግዚአብሔር እውነተኛ አምልኮን ይፈልጋል። ስለዚህ አምልኮ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ነገር ማቅረብ ነው። ታዲያ አምልኮን ለእግዚአብሔር ማቅረብ የሚገባን እንዴት ነው?

እውነተኛ አምልኮን ለእግዚአብሔር ከምናቀርብባቸው መንገዶች መካከል ሦስቱ ምስጋና፣ ጸሎትና ስግደት ናቸው።

## በምስጋና የሚገለጽ አምልኮ

- "ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ፤ ከጠላቶቼም እድናለሁ።... እግዚአብሔር ሕያው ነው፣ ጠባቂዬም ብሩክ ነው፤ የመድኃኒቴ ጠባቂ አምላኬ ከፍ ከፍ ይበል።" (2ሳሙ. 22:4፣ 47)
- "እግዚአብሔር ታላቅ፣ ምስጋናውም ብዙ ነውና፤ በአማልክትም ሁሉ ላይ የተፈራ ነው።" (1ዜና 16:25)
- "አራት ሺህም በረኞች ነበሩ፤ አራት ሺህም ለምስጋና በተሠሩት በዜማ ዕቃዎች እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር።" (1ዜና 23:5)
- "አናጢዎቹም የእግዚአብሔርን መቅደስ በመሠረቱ ጊዜ ካህናቱ ልብሳቸውን ለብሰው መለከቱን ይዘው፣ የአሳፍም ልጆች ሌዋውያን ጸናጽል ይዘው እንደ እስራኤል ንጉሥ እንደ ዳዊት ሥርዓት እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ዘንድ ቆሙ።" (ዕዝ. 3:10)
- "እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ፣ ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው።" (መዝ. 33:1)

* "እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፣ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ፣ በእርሱ እናቅርብ።" (ዕብ. 13:15)

እውነተኛ አምልኮ በምስጋና ይገለፃል ስንል እግዚአብሔር ከቸርነቱና ከምሕረቱ የተነሳ ስላደረገልን ነገር የምናቀርበው የከንፈራችን ፍሬ ነው። በምስጋና ጊዜ አብዛኛውን ሰዓት የእግዚአብሔርን ውለታ እንቆጥራለን። እግዚአብሔር ይህንና ያንን አደረገልኝ እርሱ እግዚአብሔር ነውና አመሰግነዋለሁ። እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነቱ ይህንን ሠራልኝ እግዚአብሔርን አከብረዋለሁ ስንልና በእንደነዚህ ዓይነት ጉዳዮች እግዚአብሔርን ስናመሰግን የምንመለከተው ወደ ኋላችን ያለውን እንጂ የወደፊቱን አይደለም።

የወጣንበትን ዳገት፤ የወረድንበትን ሸለቆ፤ ያለፍንበትን ወላፈንና እሳት እያስታወስን እግዚአብሔር በዚያ መካከል እንዴት እንደ ረዳንና ከዚያ እንዴት እንዳወጣን ስናስብ በምስጋና እንሞላለን። "በዚያም ቀን እንዲህ ትላላችሁ:- እግዚአብሔርን አመስግኑ፣ ስሙንም ጥሩ፤ በአሕዛብ መካከል ሥራውን አስታውቁ፤ ስሙ ከፍ ያለ እንደሆነ ተናገሩ። ታላቅ ሥራ ሠርቶአልና ለእግዚአብሔር ተቀኙ፤ ይህንም በምድር ሁሉ ላይ አስታውቁ። አንቺ በጽዮን የምትኖሪ ሆይ፣ የእስራኤል ቅዱስ በመካከልሽ ከፍ ከፍ ብሎአልና ደስ ይበልሽ እልልም በዪ።" (ኢሳይ. 12:4-6) "እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ቸር ነውና፣ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። የአማልክትን አምላክ አመስግኑ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። የጌቶችን ጌታ አመስግኑ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤ እርሱ ብቻውን ታላቅ ተአምራትን ያደረገ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። ...የሰማይን አምላክ አመስግኑ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።" (መዝ. 135:1-6፣ 26 ) ለምሳሌ:-

▶እስራኤላውያን፦ እግዚአብሔር በምድረ በዳ ያደረገላቸውን በማሰብ ያመሰግኑታል። "ጉልበቴ ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው፣ …አቤቱ፣ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው? በምስጋና የተፈራህ ድንቅንም የምታደርግ፣ በቅድስና የከበረ እንደ አንተ ያለ ማን ነው? ቀኝህን ዘረጋህ፣ ምድርም ዋጠቻቸው። በቸርነትህ የተቤዠሃቸውን ሕዝብህን መራህ፤ በኃይልህ ወደ ቅዱስ ማደሪያህ አገባሃቸው። … በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ።" (ዘፀ. 15:2፣ 11-13፣ 21)

▶ማርያም፦ ስለ አስደናቂ የማዳን ዕቅዱ በመዝሙር ስታመሰግነው «በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባህር ጣለ።» (ዘፀ. 15፡21) ብላ ተቀኘች።

▶ሐና፦ እግዚአብሔር ልመናዋን ስለ ሰማላት በመዝሙር አመስግናዋለች። "ሐናም ስትጸልይ እንዲህ አለች፦ ልቤ በእግዚአብሔር ጸና፣ ቀንዴ በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ፤ አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ፤ በማዳንህ ደስ ብሎኛል። እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና፣ እንደ አምላካችንም ጻድቅ የለምና፤ ከአንተ በቀር ቅዱስ የለም።" (1ሳሙ. 2:1-2)

▶ዳዊትም፦ በመዝሙሩ ቸርነቱን እያሰበ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር አምላኬን አመሰግነዋለሁ እያለ የሚያመሰግንበትን ምክንያት በሰፊው ዘርዝሯል።

- "በምስጋና ወደ ፊቱ እንድረስ፣ በዝማሬም ለእርሱ እልል እንበል፤" (መዝ. 94:2)

- "እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው፣ ልዑል ሆይ፣ ለስምህ ዝማሬ ማቅረብ፤" (መዝ. 91:1)
- "ሃሌ ሉያ። እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት፤ በአርያም አመስግኑት። መላእክቱ ሁሉ፣ አመስግኑት። ሠራዊቱ ሁሉ፣ አመስግኑት። ፀሐይና ጨረቃ፣ አመስግኑት፤ ከዋክብትና ብርሃን ሁሉ፣ አመስግኑት። ሰማየ ሰማያት፣ አመስግኑት፤ የሰማያት በላይም ውኃ።" (መዝ. 148:1-4)
- "ሃሌ ሉያ። እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት፤ በኃይሉ ጠፈር አመስግኑት። በችሎቱ አመስግኑት፤ በታላቅነቱ ብዛት አመስግኑት። በመለከት ድምጽ አመስግኑት፤ በበገና በመሰንቆ አመስግኑት። በከበሮና በዘፈን አመስግኑት፤ በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት። ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት፤ እልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት። እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን። ሃሌ ሉያ።" (መዝ. 150)

▶በዙፋኑ ፊት የቆሙት ሁሉ፦ ስለ ማዳን ችሎታው ሲያመስግኑ «በታላቅም ድምፅ የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት፤ ጥበብም፤ ብርታትም፤ ክብርም፤ ምስጋናም፤ በረከትም ሊቀበል ይገባዋል» ይላሉ። (ራዕይ 5፡12)

## በጸሎት መልክ የሚቀርብ አምልኮ

የምስጋና አምልኮ ውለታውን ተገንዝቦ ማድነቅ ሲሆን የጸሎት አምልኮ ደግሞ ችሎታውን ተማምኖ ሁሉንም ለእርሱ አስረክቦ በፊቱ ማቅረብ ነው።

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ወይም እግዚአብሔርን መጠየቅ ነው። እግዚአብሔር አንተ አምላክ ስለ ሆንክ ሁሉን ማድረግ ትችላለህና ይህንን አድርግልኝ ብለን በታላቁ አምላክ ፊት ስንቀርብ አምላክነቱን አምነን፤ ሁሉን ቻይነቱን ተረድተን፤ ታላቅነቱን አውቀን፤ ምህረቱን ተገንዝበን፤ ርኅራኄውንና ፍቅሩን ሁሉ ተስፋ አድርገን ነው። በጸሎት ወደ አምላካችን ስንቀርብ ብዙ ጊዜ ስላለፈው ጉዳይ ሳይሆን ስለ ወደፊቱ ጉዳይ ነው የምናስበው። ሊመጣ ስላለው ማለት ነው። "ጌታ ሆይ በፊቴ ይህ ነገር ይታየኛል ይህን አድርግልኝ" በማለት በፊታችን ሊሆን ስላለው ነገር በጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንቀርባለን። በዚህ ሁኔታ ስንጸልይ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነትና ታላቅነት አምነነው ከሆነ በዚህ ውስጥ ለእግዚአብሔር ያለንን አክብሮትና አምልኮ ገልጸናል ማለት ነው። በጸሎት በፊቱ እንድንቀርብ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በጸሎት የጠየቅነውንም እንደሚያደርግልን ብዙ ተስፋዎችን ሰጥቶናል። ለምሳሌ ያህል:-

- "ወደ እኔ ጩኽ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ።" (ኤርም. 33:3)
- "ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል።" (ማቴ. 18:19)
- "ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።" (ዮሐ. 14:14)

ወደ ሦስተኛው ከማለፋችን በፊት ከላይ በተጠቀሱት በሁለቱ ሃሳቦች ላይ ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ያለን ስህተት እንድናይ እወዳለሁ። እግዚአብሔር ምስጋናንም ሆነ ጸሎትን የሰጠን ለአምልኮ ነበር። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ምስጋናችንም ሆነ ጸሎታችን አምልኮ ያንሰዋል። ብዙውን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር

ፊት እንመጣና አምላኬን ስለዚህ ጉዳይ አመሰግነዋለሁ እንላለን። በዚያ ውስጥ ግን ምንም የእግዚአብሔር ቅድስናና፣ የእግዚአብሔር ታላቅነት፣ አይታይበትም። እግዚአብሔር ባደረገው ነገር ሕይወታችንን ከማንበርከክ ይልቅ ለዋስትና እንጠቀምበታለን። እግዚአብሔር ትላንትና ይህን አድርጓልና ነገም ይህን ያደርጋል እንላለን። ስለዚህም ዋስትናን (ኢንሹራንስ) ለመጠየቅ ብቻ ወደ እግዚአብሔር እንሄዳለን። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ በእግዚአብሔር መጠቀም ነው እንጂ አምልኮ አይደለም። አምልኮ ግን አድራጊው እግዚአብሔር ከድርጊቱ በላይ መሆኑን በማየት በፊቱ እንድንወድቅ ያደርገናል። እግዚአብሔር ያደረገው እኔ የሚገባኝ ሆኜ ሳይሆን በአምላክነቱ ነው፣ ስንል አምልኮ ውስጥ እንገባለን። እግዚአብሔር ስለ ታላቅነቱና ስለ ቸርነቱ ይህንን አድርጓልና፣ ብለን የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ቸርነት የምናውጅበት ሁኔታ አምልኮ ይሆናል። ስለዚህ ነው ዳዊት በመዝሙሩ በመደጋገም "ቸርነቱ ለዘላለም ነው" እያለ የሚዘምረው። ዳዊት ቃል አጥቶ ሳይሆን በነገሮች ሁሉ የሚያየው የእግዚአብሔርን ቸርነት ስለሆነ ነው። ይኼ ለምን ሆነ? እግዚአብሔር መሐሪና ቸር ስለሆነ ነው።

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያደረገላቸው ነገር ሁሉ ከእነርሱ ብቃት የተነሳ ሳይሆን ከአምላክነቱ የተነሳ ነበር። ስለዚህም ዳዊት እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያደረገውን ሁሉ ወስዶ ወደ አምልኮ ይለውጠው ነበር። እግዚአብሔር ከፈርኦን እጅ ነፃ አወጣን፣ ቀይ ባህርን ከፍሎ አሻገረን በምድረ በዳ መና መገበን፣ ከአለት ውኃ አፈለቀልን፣ ዮርዳኖስን አሻገረን፣ ኢያሪኮን አፍርሶ ጠላቶቻችንን አጥፍቶ የተስፋን ምድር አወረሰን እያሉ እስራኤላውያን ይህንን ውለታ እያስታወሱና እየቆጠሩ የአምላካቸውን ክንድ ታላቅነት እንዲያመልኩ አደረጋቸው። እኛም ብዙ ጊዜ በክርስትና ሕይወታችን እያደግን ስንሄድና እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሲመልስልን "እግዚአብሔር ይህንን

አደረገልኝ" ብለን ዝም ከማለት ይልቅ ይህንን ውለታውን በማሰብ በአምልኮ ፊቱ መቅረብ ያስፈልገናል። እግዚአብሔር ላደረገልን ሁሉ የሚፈልገው ምላሽ አምልኮን ብቻ ነው።

በጸሎት በኩል ደግሞ ወደ ጌታ እንመጣና «ጌታ ሆይ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህን አድርግልኝ» ብለን እንጠይቀዋለን። ጌታ ሊያደርግልን ይችላል። ነገር ግን አቀራረባችን መስጠት ያለበትና በፈሪሃ እግዚአብሔር የተሞላ መሆን አለበት። በፊቱም ስንቀርብ ለክብሩና ለታላቅነቱ መንቀጥቀጥ ያስፈልገናል። በእነዚህ ነገሮች መጠንቀቅ ያሻል። በኢየሱስ ስም ጠይቁና ታገኛላችሁ ስላለ እንጠይቃለን ብለን ነው የምንቀርበው። እግዚአብሔር በቃሉ ያለውን ነገር አምኖ መጠየቅ መልካም ነው። ለዚያም የሚኖረን መንፈሳዊ ድፍረት መልካም ነው። መንፈሳዊ ድፍረትም ሆነ እምነት ግን የእግዚአብሔርን ክብርና ታላቅነት ዝቅ ማድረግ የለበትም። ለጸሎት ተንበርክኮ እግዚአብሔርን መውቀስና እግዚአብሔርን ማማረር፣ ያልተደረገልንንና ያልሆነልንን ብቻ በማስታወስ ለራሳችን በማዘን እግዚአብሔር እንደዘጋን ሆነን መቅረብ የአምልኮ ጸሎት አይደለም። እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንድንቀርብ የሰጠን ጸጋ እርሱነቱን ዝቅ ማድረግ የለበትም። እግዚአብሔር ያንን ያደርግልኛል ስንል «ያ ነገር» እኔን ምን ያደርገኛል? ብለን ማሰብ አለብን። ያ ነገር እኔን በእግዚአብሔር ፊት እንድንበረከክና እንድወድቅ ሊያደርገኝ ይገባል። እኛ ልጆቹ ነን። የእጆቹም ሥራዎች ነን። ስለዚህም ልንሰግድለትና ልንበረከክለት ይገባል። የእርሱ መሆናችንና ፍጥረቱ መሆናችን ራሱ ሊያንበረክከን ይገባል። የአምልኮ ሕይወታችን እግዚአብሔር ስለሆነ እንደ ዘይት በዝግታ የሚፈስ የነፍስ አክብሮትና ስግደት ነው።

# ም ዕ ራ ፍ 2

◊

## በስግደት የሚገለጽ አምልኮ

- "ከምድርም ወገኖች ሁሉ ለንጉሡ ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ይሠግዱ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ለማይወጡ ለእነርሱ ዝናብ አይዘንብላቸውም።" (ዘካ. 14:17)
- "ምስጋናና ውበት በፊቱ፣ ቅዱስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸው። የአሕዛብ ወገኖች ለእግዚአብሔር አምጡ፣ ክብርንና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አምጡ፤" (መዝ. 94 (95): 6-7)
- "ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ፤ ቁርባንን ይዛችሁ በፊቱ ግቡ፤ በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ።" (1ዜና 16:29)
- "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።" (ዮሐ. 4:24)

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ምስጋናና ጸሎት እግዚአብሔርን ለማምለክ ከምንጠቀምባቸው መንገዶች ዋነኞቱ ናቸው። እንግዲህ እውነተኛ አምልኮ ከነዚህ ሁሉ በላይ ስለሆነ በሙገሳ፣ በውዳሴ እግዚአብሔርን ስለ እግዚአብሔርነቱ፣ ስለ

ታላቅነቱ፣ ስለ ዘላለማዊነቱ፣ ስለ መለኮታዊ ባሕርይ፣ ብቻ ከፍ ከፍ በማድረግ በፊቱ በስግደት መቅረብ ነው።

ስግደት ራስን ዝቅ ማድረግንና የልብ መንበርከክን ይጠይቃል። ተንበርክከን እንሰግዳለን። እውነተኛው ስግደት ከውጫዊ የአካል መተጣጠፍ (መጎንበስ) ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም። በመሠረቱ የአካላችን መውረድና መንበርከክ መልካም ነው። ይሁን እንጂ የመንፈስ መንበርከክና፤ የልብ መንበርከክ የሌለው ውጫዊ ስግደት በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ የለውም። ዋጋ የሚኖረው ውጫዊ ስግደታችን የውስጣዊው እኔነታችን ዝቅ ማለት ምልክት ሲሆን ነው። ስለዚህ ኑ እንስገድለት፤ ኑ እንበርከክለት፤ ስንል ታላቅነቱን እናውጅለት፣ የሥራው ባለቤት እርሱ መሆኑን ከልብ እናስተጋባለት ማለታችን ነው። የሚንበረከክ ሰው የተማረከ ነው። መዋጋት አይችልም። ራሱንም መከላከል አይችልም። ምክንያቱም ተንበርክኳል ጉልበት የለውም። ከእርሱ በላይ ጉልበታም የሆነ ኃይል ይቆጣጠረዋል ማለት ነው። ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት ስንበረከክ «እግዚአብሔር ሆይ ሁሉን ለአንተ አስረክቤአለሁ፤ ሙሉ በሙሉ ተማርኬአለሁ» ነው የምንለው።

- እግዚአብሔር ሆይ አንተ ብቻ ታላቅ ነህ፤
- አንተ ብቻ ቻይ ነህ፤
- አንተ ብቻ ከሁሉም በላይ ነህ፤
- ሥልጣን ሁሉ የአንተ ነው።
- በሰማይና በምድር የተከበርህ ነህ፤
- እኔ የምኖረው በአንተ ምሕረት ነው።
- እኔ የምኖረው በአንተ ጸጋ ነው።
- እኔ የምኖረው በአንተ ፍቅር ነው፤
- እኔ የምኖረው በአንተ ጥበቃ ነው ማለታችን ነው።

እግዚአብሔር የሚፈልገው አምልኮ መንበርከክን ይጠይቃል። ከመንበርከክ ጋር የሚመጣ ነገር አለ ይህም ትልቅ ነገር ነው። ከእውነተኛ የልብ መንበረከክ ጋር መሰጠት ይመጣል።

ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናት ሲሰበክልን በመስጠት እግዚአብሔርን እናመልካለን ይባላል። ነገር ግን እግዚአብሔር የምናመልከው በመሰጠት ነው። መስጠትና መሰጠት ልዩነቱን መረዳት ይገባናል። መስጠት የራስ የሆነን፣ ንብረት ወይም ሃብትን ለሌላው በነጻ ማስተላለፍ ሲሆን መሰጠት ግን ራስን መስጠት ነው። መሰጠት ከመስጠት በጣም የሚከብድና ብዙ የሚጠይቅ ነው። ብዙ ሰዎች መስጠትንም እንኳን የሚለማመዱ መሰጠት በጣም ያስቸግራቸዋል። እግዚአብሔርን የምናመልከው ግን በመሰጠት ነው ስንበረከክ መንበርከካችን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ሆይ እነሆ እኔ ያንተ ነኝ፣ ለአንተ ፈጥረኸኛል፣ ለራስህ ገዝተኸኛል፣ ለራስህ ለውጠኸኛል፣ ለራስህ አስበኸኛል እነሆኝ ጌታ ሆይ ማለታችን ነው። ይህን ስንል በራሳቸው ኃይል እጆቻችን ወደ ሰማይ ይዘረጋሉ፣ ለእግዚአብሔር ሁለንተናችን ይማረክለታል። አዕምሮአችን፣ ስሜታችን፣ ማስተዋላችን፣ መንገዳችን፣ ራእያችን፣ አገልግሎታችን፣ ሁሉ ይማረክለታል።

ይህንን በእውነት ካደረግን በኋላ፣ በእውነት እግዚአብሔርን ካመለክን በኋላ፣ ለእግዚአብሔር በእውነት ከተሰጠን በኋላ «የእኔ» የምንለው ነገር አይኖርም። አገልግሎትም፣ ራዕይም፣ መንገድም ወዘተ. ሁሉ «የእኔ» አይደለም። ሁሉ የእርሱ፣ ከእርሱ፣ ለእርሱ የሆነ ነው። ስጦታም ቢኖረኝ የእርሱ፣ ከእርሱ፣ ለእርሱ ነውና መልሼ ለእርሱ እሰጣለሁ። ለእኔ የሚገባ ክብርም የለም። ክብር ሁሉ የእርሱ ነው። ከእርሱ እኛ ሳንቀበል ለእርሱ በመስጠት ልናገለግል አንችልም። እግዚአብሔር ደግሞ ከእኛ ሊቀበል የሚፈልገው ምጽዋት ሳይሆን ሕይወታችንን ነው። እንግዲህ እውነተኛ አምልኮ ሕይወትን በመስጠት ይጀምራል።

እኛ ከተሰጠን በኋላ የእኛ የሆነውን ነገር መስጠት አያስቸግረንም። ምክንያቱም እኛ ተሰጥተናል። ሕፃናት ብቻ ናቸው የእነርሱ ያልሆነውን ዕቃ ይዘው የእኔ ነው ብለው

የሚያለቅሱት። አሥራታችንን ሳንከፍል ይዘን ብንጮህ ከሕፃናት አልተሻልንም ማለት ነው። ሕፃናት እንኳን የእናንተ አይደለም ሲባሉ እሺ ብለው ይሄዳሉ።

ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔር ነውና የእግዚአብሔርን የአምልኮ ሰዓቱንና ደቂቃውንም መስረቅ ታላቅ በደል ነው። በጊዜው ወደ ቤቱ ሄዶ እግዚአብሔርን ማምለኩ አስፈላጊ ነው። የምናመልከው አምላክ ታላቅ ጌታ ስለሆነ ሁሉ ይገባዋል። ክብሩ የሚያስፈራ፤ ገናና፤ ቅዱሳን መላዕክት በፊቱ ቆመው ፊቶቻቸውን በክንፎቻቸው ሸፍነው ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር እያሉ የሚያመልኩት የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን እኛ ለእርሱ የሚገባውን ሰዓት እንኳን ብዙ ጊዜ ከእርሱ እንሰርቃለን። የምናመልከውን በትክክል ብናውቅ ኖሮ፤ የሚጠራን ጌታ ማን እንደሆነ አውቀነው ቢሆን ኖሮ፤ አምልኮአችን ይለወጥ ነበር።

አምልኮ ከአድናቆት የሚመነጭ ውዳሴ ነው። አምልኮ የእግዚአብሔርን ቅድስና፤ የእግዚአብሔርን ንጽህና፤ የእግዚአብሔርን ታላቅነት፤ የእግዚአብሔርን ምሕረት፤ የእግዚአብሔርን ርኅራኄ ከማድነቅ የሚመነጭና ከውስጥ የሚፈልቅ ውዳሴና የነፍስ ቅኔ ነው። እግዚአብሔርን ለማድነቅ እግዚአብሔርን ማወቅ ያስፈልጋል። ያላወቅነውን ነገር ልናደንቀው አንችልም። ያላወቅነውን ነገር ብናደንቅ ውሸተኞች እንባላለን። አንድን ነገር ለማድነቅ ያንን ነገር በትክክል ማወቅ አለብን። እግዚአብሔርን ለማድነቅ እግዚአብሔርን በሚገባ ማወቅ አለብን። ለዚህ ነው ብዙ ጊዜ የአምልኮአችን ደረጃ እንደ እውቀታችን ደረጃ የሚለየው። እግዚአብሔርን ባወቅነው መጠን እናመልከዋለን። እግዚአብሔርን ባወቅነው መጠን ይበልጥ እንወደዋለን። እግዚአብሔርን ባወቅነው መጠን በፊቱ እንቀጠቀጣለን። ከዚህም የተነሣ አምልኮችአን እግዚአብሔርን ከማወቅ የሚመጣውን ቅዱስ የሆነ ፍርሃትን ያስከትላል፤

በሆነና በአክብሮት በተዋጠ ፍርሃት መቅረብ ይኖርብታል። አምልኮአችን ከማስተዋል የሚመነጭ ለእግዚአብሔር የሚገባ መሥዋዕታችን ነው።

እንግዲህ እግዚአብሔርን ለማምለክ መንፈሳዊ ማስተዋልና ዕውቀት ያስፈልጋል ማለት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ሕይወት ውስጥ የክርስትና ሕይወታችንን ምስጢር በስድስት ቁልፍ ቃላት እንመለከታቸዋለን።

- ማወቅ – እግዚአብሔርን ማወቅ
- መፍራት – እግዚአብሔርን መፍራት
- ማምለክ – እግዚአብሔርን ማምለክ
- መውደድ – እግዚአብሔርን መውደድ
- መታዘዝ – እግዚአብሔርን መታዘዝ
- መኖር – ለእግዚአብሔር መኖር

እነዚህ እንግዲህ የክርስትና ሕይወት ምስጢራት ናቸው። የእግዚአብሔር አምላካችንን ማንነት ባወቅን ቁጥር እግዚአብሔርን እንፈራዋለን እናከብረዋለን። እግዚአብሔርን በእውነት በፈራን ቁጥር በአምልኮ በፊቱ እንወድቃለን። እንሰግደለታለን፤ ከእርሱ ጋር ህብረት እናደርጋለን። በህብረታችንና በስግደታችን ውስጥ ለእግዚአብሔር እንገዛለን። ሁሉንም ደግሞ ለእርሱ እናስገዛለን። በሙሉ ልባችን፤ በሙሉ ኃይላችንና በሙሉ ማስተዋላችን እግዚአብሔርን ማምለክ እንጀምራለን። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህብረት ስለሚኖረን የእግዚአብሔር ፍቅር፤ ወደ ነፍሳችን ይፈሳል። በሮሜ 5፡5 ላይም «በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።» ስለሚል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት በምናደርግበት ጊዜ በአምልኮ የእግዚአብሔር ፍቅር ሁለንተናችንን ከተቆጣጠረ ሁለንተናችንን ከገዛ በሕይወታችን መታዘዝ ችግር አይሆንብንም። በነፃነት እንታዘዛለን። ለምን? የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና።

«ብትወዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ» የሚለው ቃል እግዚአብሔርን መታዘዝ ከፍቅር የሚመነጭ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህ ሲሆን ኑሮአችን ሁሉ ለእርሱ ክብርና ምስጋና ብቻ ይሆናል። አምልኮ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያጠቃልላል።

እንግዲህ ስለ ጠቀስናቸው ሦስቱ ነገሮች ማስተዋል የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር፦ የምስጋና አምልኮ፤ ስለተደረገልን ውለታ የሚገባውን ለጌታ ማቅረብ ነው። የጸሎት አምልኮ፤ በችሎቱ ተማምኖ ለሚያስፈልገን ነገር በፊቱ መቅረብ ነው። ምስጋናና ጸሎት መልካም ጅማሬ ሲሆን በእውነትና በመንፈስ የሆነና እግዚአብሔር የሚፈልገው አምልኮ ከዚህ ማለፍ አለበት። የአምልኮ ከፍተኛ ደረጃው እግዚአብሔር ስላደረገልን ወይም ስለሚያደርግልን ሳይሆን ስለ ማንነቱ በእውነትና በመንፈስ በሁለንተናችን እርሱን ማምለክ መቻል ነው። ይህ በልባችን (መላው ሕይወታችን) በአዕምሮአችን (ማስተዋላችን፤ ሃሳባችን)፤ በነፍሳችንና (የውስጥ ሰው)፤ በኃይላችን (ብርታታችን፤ ጉልበታችን፤ ችሎታችን፤ ጸጋችን) ማምለክ ይጠይቃል። «...ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው አንተም በፍጹም ልብህ፤ በፍጹምም ነፍስህ፤ በፍጹምም አሳብህ፤ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት።» (ማር. 12፡29) ተብሎ የተጻፈው ለዚህ ነው። እግዚአብሔርን ስለ ማንነቱ ማምለክ ከግል ልምምድ በላይ ያደርጋል። እግዚአብሔር እኔ የፈለግኩትን ወይም እኔ በፈለግሁት መንገድና በጠየቅሁት ጊዜ ቢያደርግልኝ ባያደርግልኝ እርሱ ለዘለላም አምላክ ነውና ክብር፤ ምስጋና ይገባዋል ብሎ ለእርሱ መስገድ መቻል ወደ አምልኮ ሕይወት ያሳድገናል።

ይህ ዓይነት አምልኮ ማስተዋላችንን፤ ስሜታችንን፤ ስጦታችን፤ መንፈሳዊ ብርታታችንን ሁሉ የሚጠይቅ ነው። ይህም በመሆኑ በአምልኮ ውስጥ ስሜት አለ። የልብ ደስታ፤ ሐሴት፤ እንባም (ሲያስፈልግ) ይጨመራል። አምልኮ ስሜታዊ ነገር ብቻ

ይፈልጋል። ሁለንተናችንን የፈጠረው እርሱ ለራሱ ስለሆነ ያለንን ሁሉ በመሠዊያው ላይ ማኖር ይገባናል። ይህ ነው በእውነትና በመንፈስ ማምለክ።

# ምዕራፍ 3

◊

## የምናመልከውን ማወቅ

እግዚአብሔርን ማምለክ የሚፈልግ ሰው ሁሉ የማመልከው ማንን ነው? ለሚለው ጥያቄ በቅድሚያ መልስ ማግኘት አለበት። ብዙ የምናመልካቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። አንዳንዶቻችን ሃይማኖታችንን፣ ልማዳችንን፣ አንዳንዶቻችን መልካችንን፤ ጸጉራችንን፤ አንዳንዶቻችን ዘራችንን፤ አንዳንዶቻችን ትምህርታችንን ወዘተ. ልናመልክ እንችላለን። ሌላው ቀርቶ ኃጢያትን እንኳ የሚያመልኩ አሉ። በኃጢአት የሚመኩና ኃጢአታቸውን እንደ ጀብዱ ሲተርኩ ይሰማሉ።

ክርስቲያኖች ግን የምናመልከው እግዚአብሔርን መሆን አለበት። እግዚአብሔር ኤልሻዳይ ነው። ሁሉን የሚችል፤ ሁሉን የሚያውቅ፤ በሁሉ ቦታ የሚገኝ፤ የማይለወጥ የዘላለም አምላክ ነው። ችሎታው አይመረመርም፤ መንገዱ አይታወቅም፤ ሃሳቡም ከሰው ሃሳብ በላይ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን ለማምለክ ስንበረከክ ብቻ ሳይሆን በተንበረከክን ቁጥር በአዕምሮአችን በመንፈሳችን ውስጥ የምናስበውና የምናሰላስለው በፈጣሪነቱ፤ በአዳኝነቱ፤ በአጽናኝነቱ የምናውቀውን እግዚአብሔር መሆን አለበት። ይህን ሁሉ የሆነልኝን ጌታ ነው የማመልከው እያልን ከዚህም ሌላ በሚገባ ተረድተን ልናመልከው ይገባል።

# የአምልኮአችን መሠረት

## 1. የምናመልከው እግዚአብሔር አብን ነው።

- በፍጹም ፍቅሩ የወደደንንና ልጁን የላከልንን አምላክ ነው። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሐ. 3:16)
- በልጁ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ከራሱ ጋር ያስታረቀንን አምላክ ነው። "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፤" (2ቆሮ. 5:19)
- እንደ አባታችን እንድንቀርበው የልጅነትን መንፈስ የሰጠንን አባት ነው። "ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።" (ገላ. 4:6)
- በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ልንገምተው የማንችለውን በረከት ያፈሰሰልንን የበረከት ሁሉ ምንጭን ነው። "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።" (ኤፌ. 1:3)
- ቤተሰቡ እንሆን ዘንድ በክርስቶስ በኩል የጥልን ግድግዳ አፍርሶ ቤተኞች ያደረገንን አምላክ ነው። "እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።" (ኤፌ. 2:19)

- ልጆቹ የመሆንን ሥልጣን የሰጠንን ነው። "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤" (ዮሐ. 1:12)

## 2. የምናመልከው በክርስቶስ የቃል ጸጋ ነው።

ወደ እግዚአብሔር አብ ፊት ቀርበን ማምለክ የምንችለው ደግሞ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። ያለ ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ማመለክ የሚችል ሰው የለም። ወደ አብ ፊት መቅረብ የምንችለው በእርሱ በኩል ብቻ ነው። ወደ አብ ቀርበን ማምለክ እንድንችል:-

- የኃጢአታችንን ዕዳ ከፈለልን
- በደሙ እያነጻ ዕለት በዕለት ብቃትን ይሰጠናል። "... የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።" (1ዮሐ. 1:7)
- ወደ አብ እንድንገባ መጋረጃውን ቀደደልን። "እነሆም የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ ..." (ማቴ. 27:51) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ተቀደደ። በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ ፈረሰ። (ኤፌ. 2:16)
- ወደ አብ የሚያስገባውን በር ከፈተልን። "በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፣ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል።" (ዮሐ. 10:9)
- መንገድ ሆነልን። "ኢየሱስም እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" (ዮሐ. 14:6)

- በእግዚአብሔር ፊት መቆም የሚያስችለንን ጸጋ ሰጠን። "እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና።" (ዮሐ. 1:16)
- እውነትን አስጨበጠን። የአምልኮ መሠረቱ እውነት እንደመሆኑ መጠን ጌታ ኢየሱስ ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ወደ እኛ መጣ። "... ጸጋና እውነት ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ሆነ።" (ዮሐ. 1:17)
- አማላጃችን ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዛሬ ድረስ በአብ ቀኝ የተቀመጠ ሊቀ ካህናችን እንደሆነ ይነግረናል። ሊቀ ካህን ደግሞ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ይማልዳል። ሕዝቡንም ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት ይቀርባል። አሁንም እርሱ በሰማይ ይማልዳልና ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ ያድናቸዋል። (ዕብ. 7:25) እርሱ የዘላለም አምላክና የዘላለም አምባ ስለሆነ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ይማልድልናል።
- ስሙን ሰጠን። ያለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብን ማምለክ አይቻልም። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ በታች የሚያድን ሌላ ስም የለም የሚለው ። ከኢየሱስ ስም በስተቀር (መላክትም ቢሆኑ ወይም ማንም ሥጋ ለባሽ) የሚያድን የሌለው ለዚህ ነው። ምክንያቱም የሚያድን አንድ ስም ብቻ ነው፤ በዚህ ስም ብቻ ነው ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ የምንችለው። ያም ስም ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። "መዳን በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።" (ሐዋ. 4: 12)

## 3. እግዚአብሔርን ማምለክ የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ የምንችለው በክርስቶስ ኢየሱስ ሲሆን የምናመልከው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል ነው። መንፈስ ቅዱስ በአምልኮ ብዙ ነገርን ያደርግልናል፦

- መንፈሳችንን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ያገናኛል። “ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮህ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።” (ገላ. 4:6) ያ መንፈስ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይመሰክራል። (ሮሜ 8) የመንፈስ አንድነት ከሌለን እግዚአብሔርን ማምለክ አንችልም። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገው ይህንን ነው።
- መንፈስ ቅዱስ ይጸልይልናል። እንዴት መጸለይ እንደሚገባን በማናውቅበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በማይነገር መቃተት ስለ እኛ ይጸልይልናል። የጸሎትን ሕይወትና የአምልኮን ሕይወት በውስጣችን ያፈሳል። “እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፣ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤” (ሮሜ. 8:26) አንዳንድ ጊዜ መጸለይ ካስቸገረንና ሃሳባችን ከተበታተነብን እንደዚህ ብለን እንጸልይ፦ “እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሰዓት መጸለይ እፈልጋለሁ አዕምሮዬን ተቆጣጠር” ብንል ወዲያኑ ለውጡን እናያለን፣ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ይቆጣጠረናል። መንፈስ ቅዱስ የመጣው ለዚህ ነው። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሆኖ ጌታ ኢየሱስን

እንድናከብረው፣ እንድናመልከው፣ እርሱን ከፍ ከፍ እንድናደርገው ይህንን ይሠራል።

## የአምልኮአችን ትኩረት

1. እግዚአብሔር ራሱ
    - ፈጣሪነቱ
    - ቅድስናው
    - ኃይሉ
    - ችሎታው
    - ምሕረቱ
    - ቸርነቱ
    - አባትነቱ ወዘተ.
2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
    - አዳኝነቱ
    - ፍቅሩ
    - ጸጋው
    - ጽድቁ
    - ፈዋሽነቱ
    - እረኛነቱ ወዘተ.
3. መንፈስ ቅዱስ
    - ሥራው
    - አጽናኝነቱ
    - መሪነቱ
    - ረዳትነቱ
    - ሰጭነቱ
    - አስተማሪነቱ ወዘተ. መሆን አለበት።

የአምልኮ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ ካልሆነ ልምምዳችን እውነተኛ አምልኮ አይደለም ማለት ነው። ወደ ራሳችንና ወደ ሌሎች መመልከት ከጀመርን አምልኮአችን የግብዞች አምልኮ ይሆናል። ትኩረታችን የአመላለክ ሁኔታ ላይ ከሆነ አምልኮአችን ሕይወት የሌለው ሥርዓት ብቻ ይሆናል። የአምልኮ ትኩረት ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ እግዚአብሔር መሆን ይኖርበታል።